# የአማራውን ሕዝብ ሁለገብ የሕልውና ትግል ለማገዝ መደራጀት ያስፈልጋል!

*ከኃይለገብርኤል አያሌው የቀድሞው የመዐሕድ አመራር አባል*

ለአመታት በሕዝባችን ላይ ተከማችቶ የቆየው የጭቆና አገዛዝ የፈጠረው ምሬትና ቁጣ በመላው ሃገሪቱ መፈንዳት ጀምሮል። በተለይም በኦሮምያ ባለፉት ተከታታይ ወራት የቀጠለው ሰላማዊ ተቃውሞ የአያሌ ወገኖቻችንን ህይወት እየቀጠፈ ቀጥሏል። ይህም ትግል የኦሮሞ ህዝብ ትግል ተብሎ በሃገር ወስጥና በውጭ ሚድያዎች እውቅና አግኝቷል። በተለያዩ ልዩነቶች ተብታትኖ የኖረውን የኦሮሞ ፖለቲካ ሃይሎችና ሊህቃንን አቀናጅቶ ሃገር ውስጥ ያለውን ትግል ማዕክል ያደረገ እንቅስቃሴ ሲደረግ ይታያል።

ይህ በብዛት ልሂቃኑ አክቲቪስት የሆኑበት የኦሮሞ ወንድሞቻችን እንቅስቃሴ ትግሉን በማገዝ ብቻ ሳይወስን ፤የኦሮሞውን ማህበረሰብ በማሰባሰብ የባህል ፤ የሚድያ ፤ የጥናት ክበቦችን በማቋቋም እያከናወነ ያለው ተግባር በቅርብ እያየነው ነው። ፖለቲካችን ዘውግ ተኮርነትን የተከተለ በመሆኑ ይህን አይነት አደረጃጀት ተገቢም አስፈላጊም በመሆኑ ሌሎችም ከዚህ ልንማር ያስፈልገናል።

በአንጻሩ በጎንደር ጀምሮ ባህርዳር የተሻገረው ሕዝባዊ ንቅናቄ መነሻ የሆነው ግልጽና የጠራ ማንነትን የተመረኮዘ አጀንዳ ቢኖረውም በብዛት እንደሚስተዋልው ሁሉም የራሱን ፍላጎት በሚያስረግጥ መልኩ እየገለጽው ይገኛል። ጎንደርና ባህርዳር የቦታና ፤ የክፍለሃገር መጠሪያ ስም እንጂ የሕዝብን ማንነት መግለጫ እንዳልሆነ የሚታወቅ ቢሆንም አብዛኞቹ ሚያዎችና፤ አንዳንድ አካላት ትግሉን ባለቤት እንደሌለው ፤ የጎንደር የባሕር ዳር ሕዝብ እያሉ በቦታ ስም ሲወስኑት ይታያል። እነዚህ ስፍራዎች የአማራው ሕዝብ ታሪካዊ መኖሪያ ቦታዎች እንጂ ሁኔታውንና አላማውን በቅጡ አይገልጡም ።

የአንድ ሕዝብ ማንነት መገለጫ የሆኑት መሰረታዊ የቋንቋ ፤ የባህል ፤ የስነልቦና መስተጋብሮች ሳያዛንፍና ሳያጓድል እንደ ሌሎች ብሄር ተብለው እንደትቧደኑት ሁሉ አማራውም ራሱን የሚገልጽበት ማንነት ባለቤት ነው። እነዚህ ድርና ማግ የሆኑት እሴቶች በጎጃም ፤ በጎንደር ፤ በወሎና ፤ በሸዋ ያለውን የአማራ ማሕበረሰብ አንድነት የሚያስረግጡ የጋራ ማንነቱ ማሳያ ናቸው። ጎንደሬ ጎጃሜ፤ ወለዬ፤ እና ሸዌ ተብሎ የሚጠራው አገላለጽ አካባቢያዊነትን መግለጫ የዘልማድ አገላልጽ እንጂ የዘውግ ማንነትን የሚያሳይ እይደለም።

ይህንን ሃቅ በምሁራን አካዳሚክሳዊ ትንተና ብናስረግጠው በቪዥን ኢትዮጵያ የኦሮሞ ልሂቃንን ማዕከል አድርጎ በጠራው የውይይት መድረክ ላይ ታዋቂው የፍልስፍና ምሁር ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ እንዲህ ነበር ማንነትን በተመለከተ ያቀረቡት « ዘውግ ለሰው ልጅ ማንነት ተቀዳሚና መሰረታዊ መግለጫ ነው የሚል ነው (primordialism)። የዘውግ ቀዳሚነት የሚገለጠው በደም ትስስር፤ በቋንቋ፤ በባሕል፤ ወዘተ አንድነትና ይህ አንድነት በሚፈጥራቸው ኃይለኛ ስሜቶች ነው። ይህ በስሜት የተገነባ ማንነት እራሱን ለመከላከልና ለማሳደግ ፖለቲካዊ ሉዓላዊነት ይመኛል።. . .» ሲሉ ነው የዘውገኝነትን መገለጫ ባህሪዎች የተነተኑት

አካዳሚያዊውም ታሪካዊውም ሃቅ የአማራን አማራነት ቢያስረግጥም፤ባለፉት 25 አመታት ወስጥ ይህ ነው ተብሎ የማይነገር ግፍ ሲፈጸምበት የቆየው የአማራው ሕዝብ በማንነቱ ላይ የተከፈተበትን የዕልቂት ዘመቻ ተደራጅቶ እንዳይከላከል በተለይ ምሁር ከሚባለው ወገን ሲካሄድበት የቆየው ትጥቅ አስፈቺና ነባራዊው የሃገሪቱ ፖለቲካ የሚጠይቀውን የትግል ስልትና ታክቲክ በማወሳሰብ ቀላል የማይባል ተጽኖውን አስፍኖ ቆይቷል። ከዚህም በላይ ይህን ታላቅና ሰፊ ሕዝብ ሕልውና በመካድ ውሃ በማይቋጥር ትንተና በመስጠት አማራ የሚባል እንደሌለ ለማሳመን የተደረገው አፍራሽ ተግባር ፤ ምንም አማራውን ከማንነቱ ሊነጥለው ባይችልም ፤የተከፈተበትን የተቀነባበረ የጥፋት ዘመቻ በግዜ ሊመክት የሚችል አሰላለፍ እንዳይኖረው አዘናጊ ሚና ተጫውቷል።

አማራው ማንነቱን የካዱትንም ሆነ በማንነቱ እንዳይደራጅ ሳይታክቱ የታገሉትን ልሂቃን በሃገር አንድነት አሳቢነት መዝኖ ክብሩን ሳያጎልባቸው ቆይቷል። የአማራው ገበሬ ይሁን ምሁር ፤ ከተሜ ይሁን ባላገር ፤ ከኢትዮጵያዊነት በላይ የሚቀድም ማንነት ኖሮትም ሆኖ ፈልጎ አያውቅም። ነገርግን ባለፉት ዘመናት በትግሬ ወያኔዎች በማንነቱ ላይ የተከፈተበትን የማያባራ ዘመቻ በብሄር ማንነቱ ዙሪያ እንዲነቃና እንዲሰባሰብ ግድ ብሎታል። ይህንን የተለወጠ ሁኔታ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ለመቀበል የማይፈልጉ ወገኖች የአማራ ሕዝብ ተጋድሎ እንደሆነ እውቅና የመንፈግ አቅጣጫ ሲያንጸባርቁ ይስተዋላል።

በቅርቡም በብረት ታግዞ በጎንደር የተቀሰቀሰውን የአማራ ሕዝብ ተጋድሎን አማራዊ ብሄርተኝነት ሳይሆን ጎንደራዊ የማድረግ ሰፊ የፕሮፓጋንድ ዘምቻ ሲካሄድ እንደነበር ብዙዎች ልብ አላሉትም ነበር። ይህ የሕዝቡን አንድነትና የተጋድሎ አላማውን በሂደት ሊያደናቅፍ የሚችል እንቅስቃሴ ችላ ተብሎ ሊታለፍ አይገባም። ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ ለአማራዊ ማንነታቸው ይህ ቀረሽ የማይባል መስዋዕትነት ለከፈሉት የወልቃይት ጠገዴ ጀግኖች ክብር

ይግባቸውና በመራራ ትግል እየተገነባ የጎመራውን የአማራ ብሄርተኝነት በግርግርና በጠለፋ እንዳይደናቀፍ መግታት ለነገ የማይባል ተግባር ነው።

አማራው ለትግሬ ወያኔዎችና ለሌሎች ታሪካዊ ጠላቶቹ ተጋፍጦ ለጥቃት እንዲዳረግ መንገድ ጠራጊ በመሆን ክህደት የተፈጸመበት በመጀመሪያ ሳይማር ያስተማረው ፤ሳይጠግብ የመገበው፤ከራሱ አብራክ በወጡ ልጆቹ ለመሆኑ ከትላንት ከነዋለልኝ ጀምሮ አስከዛሬ ድረስ በተለያየ መልክና ቅርጽ ሲተገበር ቆይቷል። አማራው ሰፊ የተማረ ማሕበረሰብ እንዳላፈራ በዚህ ቀውጢ ወቅት ላይ ልሂቃን ልጆቹ ተሰባስበው ትግሉን ሊያግዙ ፤ በደጀንነት ተሰልፈው አይዞህ ሊሉት አልታደለም ። የወልቃይት አማሮች መስፈሪያ የሌለው ዋጋ ለአማራዊ ማንነታቸው ከፈለው ያነቃነቁት ሕዝባዊ መዐበል ያለበቂ የምሁራን ድጋፍ ፤ በገጠር ገበሬዎችና በከተማ ወጣቶች የተቀናጀ ትግል ለመሆኑ በገሃድ የሚታይ ሃቅ ነው።

የዘመናት ብሶት የወለደው የመከራ ጎርፍ እያስነሳ ያለው ሕዝባዊ የቁጣ ማዐበል አቅጣጫ የሚያሲዘውና ሂደቱን የሚመራ አካል ካላገኘ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ቀላል አይሆንም። የአማራው ሕዝብ ጠላቶቹም ሆነ ወዳጆቹ ሊረዱት ከሚገባው በላይ ባለፉት ዘመናት ያሳየው እጅግ እልህ አስጨራሽ የታጋሽነት ጠባይ አማራው ቅስሙ ተሰብሮ በጨቋኞቹ የትግሬ ወያኔዎች ሴራ ወኔው መክኖ ለአገዛዝ የተመቸ መስሎም እስከመታየት ደርሶም ነበር። የወልቃይት ጀግና አማሮችን የመብትና የማንነት ትግል ተመርኩዞ የተቀጣጠለው የአማራው ሕዝብ አመጽ ይህ ሕዝብ የጀግንነት ባሕሉንና ወኔውን ዓለም ጉድ እስኪል በሰላምም በብረት አገዝ ሰልፍም የትግሉ ችቦ ለኩሷል።

ከፖለቲካዊ ትግልና የነጻነት ሕዝባዊ ንቅናቄ ታሪክ እንዳየነው፤ በተደጋጋሚም በራሳችን ላይ ከደረሰው ተሞክሮ እንደምነረዳው ጋብ ያለ ትግል ለቅልበሳ ፤ ያልተደራጀም ትግል ለድምሰሳ ሊጋለጥ እንደሚችል ነው። በቅርቡ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ ቁጣ በሰላማዊ መንገድና በብረት አከል ንቅናቄ በጎንደር ተጀምሮ ወደ ሌሎች የአማራው አካባቢዎች እየተዛመተ ያለው ጸረ ሕወሓት ትግል በሚያስደንቅ መልኩ እስካሁን ድረስ የዘለቀው ያለ መሪ ድርጅት በሕዝቡ የጎበዝ አለቆች አመራር ነው። ይህን መሠል አመጽ አድማሱ ሲሰፋና የትግሉ እንቅስቃሴ ሲያይል እንደ መጀመሪያው በጎበዝ አለቃ አመራር በውጤታማ መልኩ ይቀጥላል ብሎ መገመት አይቻልም።

ይህ በአማራ ገበሬዎችና ወጣቶች የተቀጣጠለው መሬት አንቀጠቅጥ ሕዝባዊ አመጽ ተገቢውን መረጃና ማብራሪያ ለውጭ ሚድያዎች የሚያቀርብ ፤ ለዲፕሎማሲው ማሕበረሰብ የሚካሄደውን ትግልና የሚፈጸመውን የመብት ረገጣ ጥራት ባለው መንገድ የሚያስረዳ ፤ ለሚደረገውም ትግል አስፈላጊውን የማቴሪያልና ፤ የሎጀስቲክ ድጋፍ የሚያሰባስብ ፤ ሁለገብ

የማስተባበርን ስራ የሚያሳልጥ አማራዊ ተቋም ለመመስረት አቅሙም ችሎታውም ያለው በውጭ የሚገኘው የአማራው ልሂቅ በመሆኑ እንደዚህ ቀደሙ ሂደቱን በዳር ተመልካችነት በጸጥታ መመልከቱን አቁሞ የወገኑን ትግል ሊያግዝ ሞራላዊም ታሪካዊም ግዴታ እንዳለብት ተረድቶ ድርሻውን ለመወጣት መነሳት ይኖርበታል ።

የፖለቲካ አቋምና ድርጅታዊ አወቃቀር ከነባራዊና ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ተዛማጅ የሚሆን እንጂ ማንም በፈለገው አቅጣጫ የሚጠመዝዘው አይደለም። የአማራው ሕዝብ ለኢትዮጵያና ፤ ለኢትዮጵያዊነቱ የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶ ፤ብዙ ታገሰ ፤ በገፍ ተጋዘ ፤ በጅምላ ተገደለ ፤ እጅግ ብዙ ግፍ ተሸከመ። ይህ ሃገራዊ ማንነት ሁሉም ብሄሮች የሚጋሩት በጎ በረከት ቢሆንም አማራው ግን ተለይቶ ብዙ መስዋዕትነት ከፈለ። በመጨረሻም ይህን ክቡርና ቅዱስ የሆነ የኢትዮጵያዊነት ማሕተሙን ሳይለውጥ አማራዊ ብሔርተኝነትን አንግቦ ተነሳ። ሲሸሸው የኖረውን የዘውግ ፖለቲካ ሳይወድ በግድ ሕልውናውን ለመከላከል እንዲላበሰው ሆነ። ከዚህ በኋላ ከዚህ ብሔረትኛ አመለካከቱ ሊገላግለው የሚችል ሁኔታ ቢኖር ፤ በዘር ማንነቱ ላይ ጦርነት ያወጀበት የትግሬ ወያኔ ቡድን መቃብር ሲወርድ ብቻ ነው።

ይህን የተለወጠ የአማራውን የብሔረትኝነት አቋምና ትግል በማጣጣል አታካቹን የዜሮ ድምር የሕብረብሄራዊነት አደረጃጀት ፍልስፍና በማቀንቀን እንቅስቃሴውን ማጨናገፍ አይቻልም። የአማራው ልሂቅ ከተጠናወተው ግለኝነትና ጥራዝ ነጠቅ ትንተና ተላቆ መሬት ላይ ያለውን ሃቅ ሊቀበልና የድርሻውን ሊያበረክት ይገባል። ማን ነው ከእናት ከአባቱ የወረስውን ማንነት የሚለውጥ? ይቻላልስ ወይ? የዘር ሐረግህ ወንጀል ሆኖ ጥፋት ሲታወጅብህ መልስህ ምንድን ነው? አያገባኝም? አይሠራም! ቅራኔው ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ አይደለም ፤ በሐሳብ ፍጭት ወይም ከአስተሳሰቡ ፤ በመራቅ ማምለጥ የማይቻልበት ፤ ተፈጥሮህ ጥፋተኛ ከተባለ ፤ የጠላትህ ጥላቻ አጥንትና ደምህ ከሆነ ፤ከቶስ ወዴት ታምልጣለህ? መልስህስ ምንድን ነው? ሊያጠፋህ የመጣውን ጠላት በጸጋ ተቀብሎ ባሪያ ሆኖ መኖር አልያስ ለነጻነትህ ለክብርህ ዘብ መቆም ፤ ይህ ምርጫ ነው ከፊታችን ያለው ፤ ይህንን መመለስ የእያንዳዱ አማራ ፋንታ ነው ።

የማይነጋ ሌሊት የማያልቅ መንገድ የማይጠልቅ ጀንበር እንደሌለ ሁሉ የማያልፍም መከራም አይኖርም። አማራው በታሪክ ከገጠሙት ጠላቶች ሁሉ በባህሪው ሆነ በአይነቱ እጅግ የተለየውና የከፋው የትግሬ ወያኔዎች ቡድን ሲያደርስበት የቆየውን የተቀነባበረ የጥፋት ዘመቻ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ በመገርሰስ ማንነቱን ይታደጋል። እስከዛሬም ሃገሩን ከጠላት ተከላክሎ መብቱን አስከብሮ ለመኖር የማንንም እርዳታ አልጠበቀም ። ዛሬም ያንን ታሪኩን

የማይደግምበት ምክንያት አይኖርም። ነገር ግን ከተለወጠው የዓለማችን ሁኔታና ከጠላቱ አሠላለፍ አኳያ የማታ ማታ ድል መቀዳጀቱ ባይቀርም የሚያስከፍለውን መስዋዕትነት ለመቀነስና ፣ተጋድሎም ለቅልበሳና ለስርዓት አልበኝነት እንዳይዳረግ ፣ ምሁራን ልጆቹ የጀመረውን ሕዝባዊ ንቅናቄ ዘመኑ በሚጠይቀው የአመራር ስልትና የቴክኖሎጂ እርዳታ እንዲያግዙት ወገናዊ ጥሪ ያስተላልፋል።

በአማራው ስም የተደራጁ ቡድኖች በተለያዩ የዓለም ማዕዘናት እንዳሉ ይታወቃል። የነዚህ ሁሉ ጥረትና ድካም ለበጎ ቢሆንም የተበታተነ ትግልና ጥቃቅን ቡድኖች በተናጥል ውጤት ለማስገኘት ስለሚከብድ አላማቸው አንድ እስከሆነ ድረስ በጋራ የማይሠሩበት ምንም ምክንያት አይኖርም። የአማራው ሕዝብ ትግል አሁን ካለበት ደርጃ ከፍ እንዲል በመግለጫና በኡኡታ አሠሚ ኮሚቴነት የተወሰኑ አማራ አቀፍና ክፍለሃገር ተኮር (የጎጃም ሕብረት ፣ የጎንደር ሕብረት )አይነት ተቋማት በአንድ የአማራ ሕዝብ ጥላ ስር በጋራ እንዲሰባሰቡ ጥሪ እየቀረበላቸው ነው።

የአማራ ሕዝብ የፖለቲካ ንቃት ከፖለቲካ ሃይሎችና ከዲያስፖራው ልሂቃን በላይ ተራምዶ የራሱን ብሔር አጀንዳ ብቻ ሳይሆን የሌሎች ኢትዮጵያውያንን መከራና እንግልት (በተለይ የኦሮሞ ወገኑን ትግል በማስተጋባት ያሳየው በሳል ንቅናቄ የሃገራችንን ሕዝቦች ትግል እንዲተሳሰር አይነተኛ ተግባር ፈጽሟል። ይህንን የሕዝባችንን ንቃትና ብቃት መሠረት ያደረገ ብስለት ያለው ድርጅትና ድጋፍ ሰጪ አመራር ፈጥሮ መንቀሳቀስ በነጻው አለም ላለው የብሄሩ ልሂቃን የሚተው ተግባር ነው።

**እግዚያብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!**

**አሜን!!!**